# በኮሎምቢያ ዲስትሪክት እሳትና ድንገተኛ አደጋ ሕክምና አገልግሎቶች

# የክረምት የእሳት አደጋ ደህንነት እና የተንቀሳቃሽ ማሞቂያ አጠቃቀም



### በነጭ ናፍጣ የሚሰሩ ማሞቂያዎች መጠቀም የተከለከለ ነው

- የኮሎምቢያ ዲስትሪክት የእሳት ደንብ በዋሺንግተን ዲሲ ውስጥ በሚገኝ ማንኛውም ቦታ ውስጥ በነጭ ናፍጣ የሚሰሩ ማሞቂያዎችን መጠቀም በጥብቅ የተከለከለ ነው።
- በነጭ ናፍጣ የሚሰሩ ማሞቂያዎች በ ኮሎምቢያ ዲስትሪክት እሳትና ድንገተኛ አደጋ ህክምና ክፍል ይወረሳሉ። ይህንን ደንብ መጣስ እስከ $300.00 በሚደርስ የገንዘብ ቅጣት ያስቀጣል።
- በነጭ ናፍጣ የሚሰሩ ማሞቂያዎች በማንኛውም ጥቅም ላይ የሚውሉበት ቦታ የእሳት አደጋ ስጋትን ከፍ እንዲል ያደርጋሉ።



### ተቀባይነት ያላቸው ተንቀሳቃሽ ማሞቂያዎች

- በኤሌክትሪክ የሚሰሩ የቦታ ማሞቂያዎች
- በኤሌክትሪክ የሚሰሩ የዘይት ወይንም የውኃ ራዲያተሮች
- በኤሌክትሪክ የሚሰሩ የቤዝቦርድ ማሞቂያዎች

### የተንቀሳቃሽ ማሞቂያ ደህንነት ምክሮች

- ማንኛውም ተንቀሳቃሽ ማሞቂያ ከመጠቀምዎ በፊት የአምራቹ የአጠቃቀም መመሪያዎችን ያንብቡ።
- እቤት ውስጥ የሚጠቀሙበት ተንቀሳቃሽ ማሞቂያ በፍጹም በቸልተኝነት ወይንም ህጻን ብቻ ባለበት ቦታ አይተዉ።
- በኤሌክትሪክ የሚሰሩ ተንቀሳቃሽ ማሞቂያዎችን በፍጹም ከሰውነት መታጠቢያ ወይንም ከውኃ አጠገብ አይጠቀሙ።
- በማንኛውም ተንቀሳቃሽ ማሞቂያ ዙርያ ቢያንስ 3 ጫማ ክፍት ቦታ መኖር አለበት።
- የኤሌክትሪክ ኃይል ማስተላለፊያ ገመድ እንዳይላጥ እና ጉዳት እንዳይደርስበት በመደበኛ ሁኔታ ይፈትሹ።
- የማቂያ ገመድ በፍጹም ከምድርቤት ምንጣፍ ስር አያድርጉ።
- ፍጹም አስፈላጊ ካልሆኑ በስተቀር ተቀጣይ ገመዶችን ከመጠቀም ይቆጠቡ።
- ተቀጣይ ገመድ መጠቀምዎ የግድ ከሆነ፣ የማሞቅያ አምራቹ ምክሮችን ይከተሉ።

### የክረምት የማሞቂያ ደህንነት ምክሮች

- ማሞቂያዎ በየአመቱ በብቁ ባለሙያ ያስፈትሹ እና አስፈላጊ ከሆነም ያስጠግኑ።
- አስፈላጊ ከሆነ፣ ጭስ ማውጪያዎ በየአመቱ ያስፈትሹ እና ያስጠርጉ።
- እሳት እየነደደ የሚገኝበት የእሳት ማንደጃ ቦታ በቸልተኝነት ትተው አይሂዱ።
- ምጣድዎ ወይንም ምድጃዎ ቤት ለማሞቅ አይጠቀሙባቸው።
- እያንዳንዱ የቤትዎ ደረጃ በሚገባ የሚሰራ የጭስ ማሳወቂያ ደወል እንዳለው ያረጋግጡ እንዲሁም ባትሪዎቹን በየ 6 ወሩ መቀየር እንዳለብዎ እርግጠኛ ይሁኑ።
- ከቤተሰብዎ ጋር በመሆን የእሳት አደጋ ማምለጫ እቅድ ያዘጋጁ እንዲሁም ይለማመዱት።

### ለተጨማሪ መረጃ፣

ወደ የኮሎምቢያ ዲስትሪክት እሳት እና ድንገተኛ አደጋ ሕክምና አገልግሎቶች እና የህይወት ደህንነት ትምህርት ክፍል በስልክ ቁጥር 202.727.1600 ይደውሉ

**John A. Donnelly, Sr.**

*የእሳት እና ድንገተኛ አደጋ ሕክምና አገልግሎቶች ሀላፊሀላፊ*